# <u>የኦነግ ግልብጥ የሌንጮ ለታ ፀረ_ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሽፍጥና የለበጣ አቋም</u>

ከአስተዋይ በቀለ

ሌንጮ ለታ፥ የተባለው አንጋፋ የኦነግ ግልብጥ ዩሃንስ ለታ ተብሎ የሚታወቅ የወለጋ ወይም የዳሞት ክፍለ ሃገር ሰው ነው። (ወለጋ የጥንት ስሙ ዳሞት ነበር የሚባለው)።

ይህ ሰው የፖለቲካ ክላውት ወይም ወታደራዊ ጉልበት ፈጽሞ የሌለው እንደ ስብሃት ነጋ እንደፈለገው የሚቀደድና የሚናቆር ችግር ፈጣሪ ልግመኛ ደማጎግ ነው።

ፖለቲካው ቀርቶ አርቆ አስተዋይ ቢሆን ኖሮ እንኳ ፣ ወያኔ በአዘጋጀው በሰኔ ጉባኤና አከታትሎም አሥመራ ላይ የሻቢያን ነፃነት በይፋ በመደገፍ ባደባባይ ባልቀለለና የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቀይሞ <u>"ማፈሪያው ሌንጮ"</u> ብሎ ባላወገዘውና እፍና ትፍ አድርጐ በጥላቻ ባልተፋው ነበር።

ኦሮሞ ኦሮሞ ይላል እንጂ እድሜ ልኩን መለስ ይሙት፥ የኢሳያስን ሥጋ ይንሳኝ እያለ በመገዘት አብሮ የኖረውና ያገለገለው ይበልጡኑ ወያኔንና ሻቢያን ሲሆን፤ ድካሙ አልባረክለት ብሎ ሥልጣንና ኑሮ ከሸፎበት በሃፍረትና በውርደት አድፍጦ ይኖር ነበር።

አሁን ወያኔንና ዘረኛ ሥርዓቱን ሊጠራርግ እንደ ዐውሎ ነፋስ እያሰፈሰፈ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ አመፅ መቃረብ ለሌንጮ ለታ ከፍተኛ ስጋት ስለሆነበት በኢትዮጵያዊነት <u>ለሁሉም ብሄረሰቦች</u> አሳቢ ሆኖ በመቅረብ <u>"ለሁሉም ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ፍትህ፣ ነፃነት፣ እኩልነትና የዴሞክራሲ መብት መከበር መታገል . . . ወዘተ."</u> በሚል ሽፋን ወያኔ_ አድን፣ ክልል_ አድን የኦሮሞ ዴሞክራሲዊ ግንባር መስርቶ የሽፍጥና የለበጣ አቋሙን በማኒፌስቶ ይፋ አድርጓል።

## ልብ በል የኢትዮጵያ ሕዝብ !

የእነ ሌንጮ የኦሮሞ ዴሞክራሲዊ ግንባር በተንኮታንኮተው ኦነግ መቃብር ላይ ያቆጠቆጠ፣ የወያኔ_ኦነግን ራእይና የብሄር ዘረኛነትን <u>የሚንከባከብ</u> ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን <u>"ኢምፓየራዊ ሥርዓት"</u> አድርጐ የሚከስ መሰሪ አቋም ሲሆን ማኒፌስቶው ሲሰመርበትና በሚገባ ሲጤን ደግሞ ወያኔ ጥሩ ስርቷል አይገርሰስ፣የሚያስፈልገው <u>የፌዴራል ሥርዓቱን አተገባበር አርመን ክልሎችንና የዘር ልዩነታችንን ጠብቀን የራሳችንን ዕድል በራሳችን መወሰን ተገቢ ነው</u> ይልና <u>ከወያኔ ጋር አብረን እንስራና ሕብረ_በሔራዊ ፌዴሬሽን እውን እናድርግ</u> በማለት ጥሪ ያቀርባል።

ስለሆነም ሰሞኑን ይህን የተንኮልና መሰሪ ሥራውን እንደ ልማዱ ሎሌነት ከጌታው ከወያኔ ጋር ለማድራትና ለመሾረብ ወደ አዲስ አበባ እያቀና ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው ደግሞ ወያኔን መገርሰስ፣ ሥርዓቱን ማፍረስ፣ የዘር ክልሎችን ማጥፋት፣ አገርን ማዳን፣ የሕዝብና የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ. . . ወዘተ. ነው።

ስለዚህ የሌንጮ ለታ የለበጣ አቋሙና ያቋቋመው የዘር ግንባር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጐትና ብሔራዊ ጥቅም ጋር በተጻራሪነት የቆመ አፍራሽ እንጂ በኢጋርነት በፀረ_ ወያኔ ትግል በኢትዮጵያ ሕዝብ ታምኖ አብሮ የሚሄድ አይደለም ።

ስለሆነም ሌንጮ ለታ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አሳቢ መስሎ ወያኔንና ዘረኛ ሥርዓቱን ከሕዝብ አመፅ ለማዳን በወሰደው ሴረኛ አቋሙ እርሱና የመሰረተው የኦሮሞ ዴሞክራሲዊ ግንባር በዐውሎ ነፋስ ፊት እንዳለ ገለባ መሆናቸውን መረዳት አለበት።

## የኢትዮጵያ ሕዝብ አመፅ ያሸንፋል ! !

02/05/15